ኢትዮጵያዊ ጥምር ማንነት፤
ለአንድነት ሕዳሴ የሕዝብ ጩዋነት፤
ይፋ ሆኖ ወጣ በምርጫው ዕለት፤
ታሪካዊቷ ዕለት ግንቦት ፲፭ት፤
፳፻ ወ፪ቱ ዓመተ ምሕረት።

**በስቡሕ**



| ታ.ቊ. | ይዘት | ገጽ |
|---|---|---|
| ክፍል ፩፦ | ሀገራዊ ጥምር ማንነትና ስሜት | ፫ |
| ክፍል ፪፦ | ልብ ላለው ሰው ላስተዋለው፤<br>ሰው መሆን ራሱ ሕግ ነው። | ፮ |
| ክፍል ፫፦ | ታጥቦ ጭቃ ግልገሉ ልዑል፤<br>መድረክ ላይ ሲንከባለል። | ፰ |
| ክፍል ፬፦ | የአቶ ስዩ ፖለቲክስ | ፲፩ |
| ፍጻሜው፦ | የባለ ብዕሩ ልሳን | ፲፫ |



## ይህነን ለመጻፍ ያነሳሱኝ ሁነታዎች፦

፩ኛ. የምርጫው ሰላማዊ መሆን፦

ሀ. ለኢትዮጵያ ሕዝብ ምስጋና ለማቅረብ
ለ. ደስታየን ለመግለጽ

፪ኛ. በኢትዮጵያዊነት ጥምር ማንነት (NATIONALISM) በሀገራዊነት ስሜትና በብሔር ብሔረ ሰቦች ታሪካዊ አንድነት ላይ ያለኝን ግንዛቤና የመሰለኝን ሐተታ ወገኖቼን በጽሑፍ ለማወያየትና ለመማር፤

፫ኛ. የተቃዋሚ ጎራ ትርምስና የታጥቦ ጭቃ ፖለቲካን በተመለከተ ዲያስፖራዊ ትዕዝብቴን ለመግለፅ፦

፬ኛ. <<…እምቃልከ ትጸድቅ ወእም ቃልከ ትትኴነን>> ያለው መጽሐፍ ለካስ እውነት ነው። አቶ ስዩ አብርሃ <<…እኛ የብሔር ብሔረ ስብ ከረጢት አይደለንም …>> ሲሉ በተናገሩ ጊዜ፣ በንግግራቸው ብቻ ሳይሆን በአነጋገራቸውም ጭምር፥ በውስጤ የጫሩብኝ ነገር <ቁጣ!> ባልለውም እንኳ ያሳደሩብኝ አሉታዊ ስሜት ግን ምንም ልደብቀው አልችልም። በሳቸው ላይ የነበረኝ ክብርና ፍቅር ሁሉ ሚሸሹብኝ። ስለዚህም ስሜቴን በጽሑፍ መልክ ልግለፀው ብዩ ነው።

ዕለት፦ ኀምሌ ፪ት፥ ፳፻ወ፪ቱ ዓ/ም

መልካም ንባብ >>>>>>

## መግቢያ፦

በኢትዮጵያ የ፳፻ወ፪ቱ ዓ/ም ፬ኛው ሀገራዊና ክልላዊ ምርጫ በሰላም በመጠናቀቁ የተሰማኝ ደስታ ወሰን የለውም። ምርጫው ሰላማዊና ሕጋዊ ሊሆን የቻለው ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ምርጫ ብቻ እንዲሆንና የውጭ ጣልቃ ገብነትን ለማስወገድ በተደረገው ያላሰለሰ ትግል ምክንያት መሆኑ ግልፅ ነው። ይህ ድል ደግሞ ራሱ በኢትዮጵያ ነጻነትና ልዕልና ያለመደራደር፣ የአባቶቹን ሱሪ በታጠቀው ጅግናው ታጋዩ ትውልድ አኩሪ የተጋድሎ ሥነ-ጥበብና ሥራ ውጤት በመሆኑ ለታጋዩ ማኅበረ ሰብ ክብርና ምስጋና ይድረሰው፤ ኮርቶ አኩርቶናል። በተለይ ለዲያስፖራ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያ፣ ምርጫው ሰላማዊ መሆኑ የመንፈስ እርካታና ሞራል የሠጠን ይመስለኛል።

ለኢትዮጵያ ሕዝብ ክብር፥ መስጋና ይድረስውና፣ እንግዲህ፥ WHER ARE YOU FROM? ብለው ሲጥይቁን፣ ቀና ብለን ኮርተን፣ ተዝናንተን፣ WE ARE FROM ETHIOPIA ለማለት አስችሎናል። በሕዝባችን አስተዋይነት፥ ብልህነትና ጨዋነት ተማምነን፣ እንግዲህ፥ በሰላም እጦትና በድኽነት ምክንያት፣ የሚደፋ ኢትዮጵያዊ አንገት አይኖርም የሚያሰኝ ብሩህ ተስፋ ለማየት አብቅቶናል።

በበኩሌ በቅኝ ግዛት ባልተነካውና ባልተበከለው ድንግል ሀገረ ኢትዮጵያ ሕዝብ ጀግንነት፥ ብልህነት (WISDOM፣) አስተዋይነት፥ ሰላማዊነት፥ ትዕግሥት፥ መቻቻልና ጨዋነት ከመቼውም ጊዜ በላይ ኮርቼአለሁ፤ ደስ ብሎኛልም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ እያደረገ ባለው ፀረ ድኽነት ርብርብ ላይም በኢህአዴግ መሪነትና አስተባባሪነት፣ ድል-በድል እንደሚወጣው ጥርጥር የለውም። ድኽነት ለመቅረፍ ብሎም ለማጥፋት በሚደረገው ወሳኙ ፊልሚያ መሳተፍ ወይም ያለመሳተፍ ግን ለሐቀኛ ኢትዮጵያዊነትና ሀገር ፍቅር ወኔ የፖለቲካው ሰውነት ጤናማነት፦ ትኩሳቱንና ንረቱን መርምሮ ለማወቅ የሚስችል ትክክለኛ መሣርያው ይህ ይመስለኛል።

እኔ ለአገሬ ምን ሠራሁ ነው እንጂ አገሬ ምን ሠራችልኝ አይባልም "Ask Not What Your Country Can Do For You" አሉ J.F. Kennedy ይባላል፤ እናም፥ ሠራተኛ ሁኖ መገኘት ነው እንጂ ወሬኛና ወረተኛ ሆኖ መገኘት ምን ዋጋ አለው። እንዲያውም፥ ሺ ጊዜ ከኔ ወድያ ኢትዮጵያዊነት ላሳር እያሉ በተግባር፥ በሀገር ግንባታ ሥራ ግን ዜሮ ከሆኑ፣ ከሥራ የተለየ እምነት ወይ አያሾም ወይ አያጸድቅ ዓይነት ከንቱ ድካም፥ ከንቱ ጥረት ነው፤ ፋይዳም የለውም።

ወደ ዓውደ ንባቡ አብረን እንቀጥል >>>>>>

ኢትዮጵያዊ ጥምር ማንነት፤
ለአንድነት ሕዳሴ የሕዝብ ጨዋነት፤
ይፋ ሆኖ ወጣ በምርጫው ዕለት፤
ታሪካዊቷ ዕለት ግንቦት ፲፭ት፤
፳፻ ወ፪ቱ ዓመተ ምሕረት።

በስቡሕ

## ክፍል ፩፦ ሀገራዊ ጥምር ማንነትና ስሜት፦

ኢትዮጵያዊነት ጥምር ማንነትና ስሜት *(NATIONALISM: COLLECTIVE IDENTITY)* ማለት ሀገራዊነት በአንድነት፥ በውህደትና በጨዋነት መልኩ ሲተረጎም፣ ልዑላዊ ሕዝብ ማለት ይመስለኛል። ብሔር ብሔረ ሰባዊ ማንነትና ስሜት ማለት ደግሞ ጠቅላላ ማኅበረ ሰባዊ ስሜትና ማንነት በኢትዮጵያ መልክዐ ምድር የሚገኝ ልዩ ሀገራዊ ጸጋ ማለት ብቻ ሳይሆን ለኢቲዮጵያ ጥንታዊ ታሪክ ዋና ሥረ-መሠረት ውስጠ ምሥጢሩ፥ እሱ፥ ራሱ፥ ባለቤቱ ሕዝቡ ነው ቢባልም ትክክለኛ ፍችና አተርጓጐም ይመስለኛል። በሌላ ምሳሌአዊ አነጋገር ሲታይ ደግሞ ኢትዮጵያ የሚሏት ዕፀ ሕይወት፥ ሥር፥ ግንድና ቅርንጫፍ፥ ሦስት አካላት ቢኖሯትም፣ አንድ ዕፅ ናት። በልምላሜዋና በውበቷ፥ በኅብረ አበቧ፥ የአከባቢ ዑቃቤ፥ መልክና ግርማ ሞገሥ፤ ለሰዎች፥ ለወፎች፥ ለእንስሳት፥ ለፍጡራን ሁሉ ሲሳያቸው ናት፤ ያርፉባታል፣ ይመገቧታልም፤ ኢትዮጵያም እንዲሁ ናት። ብሔር ብሔረ ሰቦቿ የየራሳቸው ባህል፥ ልምድ፥ ቋንቋ፥ ሥነ-ማኅበረ ሰባዊ እሴትን ይዘው፣ ሁሉም በጥምረት አንድ አካል፥ አንድ ሕዝብ ያላት ሀገር መሆኗን ያመለክታሉ። ስለዚህ ኢትዮጵያዊ ስሜትና ሀገራዊ ጥምረት የብሔር ብሔረ ሰብ ሕዝቦች የጋራ እሴት (Shared Value) ነው፤ ምንም ጥርጥር የለውም።

ይህ ብቻም አይደለም፦ ኢትዮጵያ ማለት የሰው ዘር መገኛ፣ የሥልጣኔ ፋና ወጊ፣ በሕግና በሥርዓት የሚኖር ጨዋ ሕዝብ ያላት ሀገር መሆኗ በታሪካዊ የሥነ-ፍጥረትና የስልጣኔ ቅሬተ አካል ግኝት ብቻ ሳይሆን፣ ዛሬም በግሃድ ፍንትው ብሎ የሚታይ ሐቅ ነው። ይህነን መካድ አይቻልም፤ ሐወልቱ ቆሞ እየመሰከረ፤ ስለ ቅሬተ አካሉ፣ የሰው ዘር ሁሉ እናት የሆነችው ሉሲ ራሷ እየመሰከረች፤ ከሥነ-ጽሑፍ እስከ ሥነ-ከዋክብት ጥናታዊ ምርምር ድረስ፥ ኢትዮጵያ ራሷን የቻለች ብቸኟ አገር መሆኗ ግልፅ ነው። በአንክሮ፣ በተዘክሮ፣ በልብ ወበ ለብዎ ማየት ከተቻለ፣ አራተኛው ዙር ሀገራዊ ምርጫ ሕጋዊና ሰላማዊ ሆኖ መጠናቀቁ፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ዓቢይ ትርጉም አለው። በተለይ ሕዝቡ ጨዋነቱ፥ ሕጋዊንቱ፥ ሐቀኛ ምንነቱና ማንነቱ ከማረጋገጡም በላይ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ እውነተኛ ወዳጆቹና ምንደኛ ጠላቶቹንም በውል መለየት የቻለበት መልካም አጋጣሚ ከመሆኑም በላይ፣ ፬ኛ ሀገራዊ መርጫ፥ ታሪካዊም ነው። ምክንያቱም ያለፈውን ገጽታ ለውጦታል፤ ኢትዮጵያ ለውጭ ጣልቃ ገብነትና ተፅዕኖ ያለመንበርከኳም ተረጋግጧል። በዚሁም እስከ ዛሬ ድረስ ያቀረቀረው አንገት ሁሉ ከያለበት ቀና-ቀና ማለት ጀምሯል።

የኤውሮጳውያን አጠቃላይ ዘረኛ አመለካከት በወኪሎቻቸው በእነ ወ/ሮ አናጎሜዝ (MS ANA GOMES)ና ህዩማን ራይት ዎች (HRW) በኩል፥ ሕጋዊውና ሰላማዊውን ምርጫ በምቀኝነትና በውሸት ጥላ ሸት ቀብተው እንከን ሊያወጡበት የሞከሩበት ምክንያትም ግልጥልጡ ወጥቷል። በአጠቃላይ በስዉር ቅኝ አገዛዝ አፍሪቃን

ዳግም ለመቆጣጠር ያላቸውን ሕልም፥ ምኞትና ሕቡዕ አጀንዳ ከማንፀባርቃቸውም ባሻገር በአፍሪቃ ሕዝብ ላይ ንቀትና ጥላቻ ያሳደረባቸውን ስካር ገና ያልወጣላቸው መሆኑንም የተሰተዋለ ይመስለኛል።

የአፍሪቃ ሕዝቦች ከያሉበት አቅጣጫ ሁሉ ለፍትሐዊ ምጣኔ ሃብት ክፍፍል፥ ለዕድገት፥ ለፍትሕ፥ ለርትዕ፥ ለእኩልነት፥ ለዲሞክራሲ፥ ለሙብትና ለነፃነት የሚያደርጉትን ትግል ሁሉ በማናናቅ፣ ምዕራባውያን (Ethnic cleansing) (ትራይባል ወር) (Tribal war) …የጎሳ ጦርነት እያሉ ይቀልዱበታል። በእነርሱ አባባል Ethnic and/or Tribal ማለት ደግሞ ያልሠለጠነ ብቻ ሳይሆን መሠልጠን የማይቻለው የብረሃ አውሬ ዓይነት፥ እርስ በራሱ የሚባላ፣ የሚናቆር፤ አንድነት የሌለው፣ የተበታተነ፤ በጦርና በቀስት የሚተላለቅ፣ ጦረኛ፥ ማለታቸው ነው። ግጭት ሲከሰት ደግሞ ወድያውኑ ሞቅ ደመቅ እንዲልላቸው ነዳጅ ያርከፈክፋብታል። የአፍሪቃውያን መተራመስ፣ መለያየት፣ ጦርነት፥ እልቂት፥ ርሃብ፥ እርዛት፥ መከራና ስቃይ፥ ለኤውሮጳውያን ምናቸው አይደለም፤ እንዲያውም የሚዝናኑበት (Entertainment) ይመስለኛል።

ወ/ሮ ማርያ አና ጎሜዝና እነ ሀዩማን ራይት ዎች (HRW) ሁሌ ከሚሰነዝሯቸው መሠረተ አልቦ አስተያየቶች መረዳት እንደሚቻለው፣ በኢትዮጵያ ፴ኛው ሀገራዊና ክልላዊ ምርጫ በሰላም በመጠናቀቁ በጣም አዝኗል፤ ማዘንም ያለባቸው ይመስለኛል። ምክንያቱም በላይ በሰማይ ሳተላይት ካሜራ ደግነው፤ በታች በምድር ደግሞ በርካታ ምርጥ-ምርጥ ፎቶግራፍ አንሺዎችንና ጋዜጠኞንች አሰማርተው፤ በብዙ የገንዘብና የቁሳቍስ ፍሰት የኢትዮጵያ ሕዝብ ደም ሲፋሰስና ሲተላለቅ እየተዝናኑ ሪፖርት ለማድረግ፤ (Documentary film) ዘመናዊና አዝናኝ ሙቪ ለመቅረፅ ያቀዱት አቅድ´ኮ ከሽፎባቸዋል። ሌላም ኢትዮጵያ ቀድሞውኑ የኤውሮጳውያኑ ቅኝ ግዛታዊ ቀንበር የሰበረች ስለሆነ ያደረባቸው ቂም-በቀል ቁርሾም አለ። ኢትዮጵያ ትፈርሳለች፣ ትፈረካከሳለች፣ ብለው ሲጠባበቁ ደግሞ አንድነቷ ይበልጥ ተረጋገጠ፤ ፈጣን ልማት፥ ሰላምና ዲሞክራሲ ሥር እየሰደደና እየተጠናከረ መጣ፤ የኒኦይዝም ፍሬ ቢስና ኢሮ…ፍልስፍና ሁሉ፦ *(LIBERALISM, NEOLIBERALISM, CONSERVATISM, EXISTENTIALISM, MOISM, LENINSM, SOCIALISM, COMMUNISM, and BLA-BLA…ISM, valueless Erotica trash philosophy)* ቅዝምዝም፥ ቅዠትና የተውሶ ርዕዮተ ዓለሙን አሽቀንጥራ ጣለች፤ የዓለምና የሀገር ውስጥ ነባራዊ ሁኔታ፥ ምጣኔ ሃብት፥ ቴክኖሎጂ፥ ትምህርትና ዘመናዊ ሥነ-ጥበብ ታሳቢ በማድረግ፣ ኢትዮጵያዊ በሆነው ርዕዮተ ዓለም፥ በአብዮታዊ ዲሞክራሲ መርሕ፥ ትመራለች፤ እናም፥ ይህ ለእነርሱ እንደ አንድ ትልቅ አደጋ የታያቸው ጉዳይ ይመስለኛል። ምክንያቱም ኢትዮጵያ በዚህ መልኩ ከእነርሱ ፈቃድና ቍጥጥር ውጭ ከመሄዷም በላይ፣ የምናልባት ሌሎቹን አፍሪቃውያን ሀገሮችንም እንዲሁ ታስተምርብናለች፤ አፍሪቃን ዳግም በቅኝ ለመግዛት ያሰብነውን ጉዳይ ሳንፈፅም በሩን ታዘጋብን ይሆናል ከሚል ካደረባችው ስጋት የመነጨ ሊሆን ይችላል። በአጠቃላይ *<<ይህች ባቂላ ካደረች አትቆረችምም>>* ዓይነት ፍራቻም ነው። ይህም የጸሐፊው ግምትና በይነ ትዝብት ብቻ ሳይሆን ባብዛኛው አንባብያንም በየራሳቸው እሳቤ የሚጋሩት አመለካከት ይመስለኛል።

ዛሬ በጊዜአዊ ሥልጣኔአቸውና በጉልበታቸው የሚመኩብን አገሮች እንደ ሀገር ሳይሆን የሚኖሩበትም ክፍለ ዓለም እንኳ ገና፣ ገና ሳይገኝና ሳይዳሰስ፣ እኛ ኢትዮጵያውያን ግን ንግሥታትና ነገሥታት (መንግሥታት) ነበሩን። የሰው ልጅ ሥልጣኔና ዘመን በፈቀደው መልኩም በሕግ እንተዳደር ነበርን፤ አሁንም ምንም ቢሆን ያንን አላጣነውም፤ እነርሱም ይህንን ያውቃሉ። ታድያ ዛሬ በማያገባቸው በሀገራዊ ጉዳዮቻችንና በምርጫችን ጣልቃ እየገቡ፣ ጣት በመቀሰር፣ እኛ ካልመሰከርንና ካልታዘብን፣ በእኛው ይሁንታና ፈቃድ

ካልሆነ በስተቀር ምርጫችሁም ሆነ ሥራችሁ ሁሉ ትክክል አይሆንም እስከ ማለት እንዴት ደፈሩን? በኢትዮጵያ በኩል ደግሞ እንመስክር ካላችሁ፣ ታዛቢ ምስክር (ALIBI WITNESS) መሆን ይቻላልና እሺ፣ ይሁን። ‹‹መስክር እንጂ ፍረድ አልተባልክም›› የሚል ኢትዮጵያዊ ብሂል አለንና ያያችሁትን፣ የታዘባችሁትን፣ እውነቱን መስክሩ፤ ፍረዱ ግን አልተባላችሁም። ምርጫው የኢትዮጵያውያን ምርጫ ነው፤ የመፍረድና የመቆጣጠር ሥልጣን ያለውም ባለጉዳዩ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንጂ እናንተ´ስ አይመለከታችሁም፤ ለዚሁም አልተጠራችሁም፣ የሀገሪቱ ሕግም አይፈቅድም መባሉም ተገቢና ሕጋዊ ይመስለኛል።

በሕጉ መሠረት፥ ተመራጭ በተመራጭነቱ፣ መራጭ በመራጭነቱ፣ ታዛቢ በታዛቢነቱ፣ ሁሉም በሚመለከተው የሥራ ዘርፍ ሓላፊነቱን ሲውጣ፣ ይኸው! ውጤቱም ያማረ፣ የሠመረ ይሆናል። በአጠቃላይ ፬ኛው ሀገራዊና ክልላዊ ምርጫ በሰላም ብቻ ሳይሆን በድል ሊጠናቀቅ የቻለውም በዚህ ምክንያትና በሕዝብ ተሳትፎ ነው። ለወደፊቱም ከዚህም ካለፈውም በመማር ሀገራዊ ክብራችንን የሚዳፈረን ሁሉ ገና በሩቁ መከላከል ግን የመንግሥት ሓላፊነት ብቻ ሳይሆን የሁሉም ዜግነታዊ ግዴታ ይመስለኛል።

## ክፍል ፪፦ ልብ ላለው ሰው ለስተዋለው፥ ሰው መሆን ራሱ ሕግ ነው።

እንደ ማኅበረ ሰባዊ ባህል፥ ልምድና ትውፊታዊ ውርሻችን፣ ለኛ፥ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሰው መሆን ራሱ ሕግ ነው። አዎ! በመጤው ሰርጎ ገብ እንግዳ ባህልና እምነት፥ በባዕዳን ትምህርትና በሆድ አደርነት፥ አእምሮው የተሰለበ፣ ክብሩን የሸጠ ሰው ካልሆነ በስተቀር፣ ለኛ ለኢትዮጵያውያን ጥንትም ዛሬም የሕግ የበላይነት እንግዳ ነገር አይደለም። በትሕትና፥ በፍቅር፥ በብሩህ ገጽ እንግዳ መቀብልና ሥነሥርዓት ማክበር ከኢትዮጵያዊነታችን ጋር ጥብቅ ውህደትና ቍርኝት አለው።

ይህ በተደጋጋሚ እንደ ወርቅ በእሳት የተፈተነው ሀገራዊ ኢትዮጵያዊ ጥምር ማንነት ዛሬ ወርቅነቱ፥ ጥንካሬው፥ አይበገሬነቱ፥ ሕጋዊነቱ፥ ጨዋነቱ፥ ወኔውና የነጻነት ስሜቱ፥ ድንገት ወደ ጠጠርና አመድ ሊለወጥ አይችልም። ጠጠር ምን ጊዜም ጠጠር ነው፣ ወርቅ ግን ምን ጊዜም ወርቅ ነው። ወርቅ በእሳት ቢፈተንም ሁሌ ጠርቶ ይወጣል፤ ወርቅነቱም በዚሁ ይታወቃል። እንዲያውም ሕገ መንግሥት ቢኖርም ባይኖርም እንኳ፤ ለምሳሌ ዓንቀፅ 39ኛ ቢወጣም ባይወጣም፣ በኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነትና ጥምር ማንነት ላይ ምንም ጫና አይኖረውም። በርቁም በቅርብም፥ የትም ያሉት ጠላቶች ሁሉ ተስፋ ይቍረጡ፤ ኢትዮጵያ አትፈርስም፣ አትፈረካከስም። ምክንያቱም ኢትዮጵያ ማለት ወንዝ፥ ተራራና ሸንተረር ሳይሆን፣ ታሪካዊ የህዝብ ጥምር ማንነት፥ አይደፈሬነት፥ ጀግንነት፥ ፅናትና አንድነት ማለት ይመስለኛል። ታሪካዊ አንድነትና ሀገራዊ ጥምር ማንነት ውርሻችን ነው። ከውጭም ከውስጥም ኢትዮጵያን ለማፍረስ የተሜረው ሤራ ሁሉ እስከ ዛሬ ድረስ አልሠራም፤ ምን ጊዜም ቢሆን አይሠራም። ምክንያቱም ታሪክ ባጭሩ ይገልፀዋል።

፮ኛ. በኢትዮጵያ የታሪክ ማኅደር የጨለማው ዘመን ተብሎ በሚታወቀው፣ በዘመነ መሳፍንት፥ ማለትም ከ1769 እስከ 1855 ዓ/ም፥ ለ86 ዓመታት ያክል ማእከላዊ የአፄ መንግሥትና በትረ መዊእ በተዳከመ ጊዜ፣ የአከባቢ ተወልጄ ነጣጥለው በያሉበት ለመግዛት ቢሞክሩም የሕዝብ መሠረታዊ ጥምር ማንነት፥ የሕዝቦች ጥምረትና አንድነት ምንም ሊፈርስ ወይም ሊዛባ አልቻለም ነበር። በዚያው በጨለማው ክፉ ጊዜ፥ የሥልጣን ሱሰኞች የየራሳቸው የግዛት ወሰን ማስፋትና ለያይተህ ግዛ እንጂ ስለ ሀገር አንድነት ግድ ባይኖራቸውም፣ የሕዝቡን አንድነት ግን ሊፈታተኑ አልቻሉም ነበር ማለት ነው። ኢትዮጵያ በዚያ በጨለማ ዘመን እንኳ አልፈረሰችም፤ ዛሬም እንሆ ኢትዮጵያ፥ በመገንባት ላይ ናት እንጂ በመፈራረስ ላይ

አይደለችም። ለወደፊትም ቢሆን የተጀመረው የመሠረተ ልማት ግንባታው አይሎ ትበለጽጋለች፣ ታድጋለች፣ ትጠነክራለች እንጂ ምንም ቢሆን አትፈርስም። ከታሪክም ካለው ከነባራዊው ሁኔታም በመማር ኢትዮጵያ ጥፋቷን የሚመኙ ሁሉ ተስፋ ይቍረጡ። አገር ውዳድ ወገን ደግሞ ደስ ይለው ይገባል።

፪ኛ. በተደጋጋሚ የውጭ ወራሪዎች በመጡበት ጊዜም ሁሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነቱን፥ ፅናቱንና ጥምር ማንነቱን አረጋግጧል። ወራሪዋ ጣሊያን በመጣች ጊዜ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር እስከ ዳር፥ በአገር አቀፍ ደረጃ በጋለ ሀገራዊ ወኔና ስሜት፥ ቆፎው እንደ ተነካበት ንብ አንድ ላይ ሆ ብሎ ለነፃነቱ ተሰውቷል። በማንኛውም ጊዜ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰብአዊ መብቱን፥ ክብሩን፥ ሀገራዊ ነፃነቱን፥ ዳር ድንበሩን፥ ልዑላዊነቱን አሳልፎ አይሰጥም። በቅርቡ አምባ ገነኑ የኢሳይያስ መንግሥት  በእብሪት ልዑላዊነታችንን ደፍሮ፣ ዳር ድንበራችን ጥሶ፣ በባድመ በኩል በወረረን ጊዜ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሳየው ቁጣና የከፈለው መስዋዕት ሁሉ ማስታወስ ይገባል። ስለዚህ በአትኩሮት ላሰበው ሰው፣ ኢትዮጵያዊ ማንነት፥ ሀገራዊ ወኔ፥ ስሜትና የሕዝብ አንድነት ጠላት የማያውቀው እምቅ፣ ድብቅ ማኅበረ ሰባዊ እሴት ነው ።

የኢትዮጵያ ጠላቶች ይህነን ኢትዮጵያዊ ማኅበረ ሰባዊ ትስስር ለመስብር ለዘመናት ሌት ተቀን ቢሞክሩም ምንም አልተቻላቸውም። እነርሱ የሚታያቸው ሕዝቡ በተላያየ የሀገሪቱ መልክዐ ምድር መስፈሩ፤ የየራሱ ቋንቋ፥ ባህልና ወግ ያለው ሕዝብ መሆኑ ብቻ ነው።  ጠላቶቹ ልዩነቱ እንጂ ምንም ሀገራዊ አንድነቱን፥ ማኅበራዊ ትስስሩን ማየት አይቻላቸውም። ምክንያቱም ከዓይን እይታ ተሰውሯቸዋል ማለት ነው። ስለዚህ ኢትዮጵያን የሚተነኳኰሉ ሁሉ ነገ ከነገ ወድያ ትፈርሳለች እያሉ በከንቱ ሲቃዡ ይኖራሉ። የኃይል እርምጃ ወስደው ለማፍረስ ሲሞክሩ ደግሞ የሐፍረት ሻማ ተከናንበው፣ ተዋርደው፣ አፍረው፣ ከስረው ይመለሳሉ። ስለ ዚህም ታሪክ ይመስክር፦ ቱርክ፥ ግብፅ፥ ጣልያን በቅርቡ ደግሞ ህግደፍ የኢረትራው መንግሥት፥ ማለትም የኢትዮጵያ ጠላቶች በሙሉ የገጠማቸው ችግር ይህ ሳይሆን አይቀርም።

የኢትዮጵያውያን ጠንካራ ማኅበረ ሰባዊ ትስስር፣ ሀገራዊ ነፃነትና ልዑላዊ ስሜት፥ አትንኩኝ ባይንትና ወኔ፣ ፍቅርና ጨዋነት ሁሉ በአሸዋ ላይ የተመሠረተ፣ የእምቧይ ካብ አይደለም። በመሆኑም የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት ሊንድና ሊያፈራርስ የሚችል ኃይል ሊኖር አይችልም። ምክንያቱም ብሔር ብሔረ ሰባዊ አንድነት ሰው ሠራሽ ወይም እንደ ሸክላ እቃ ጥፍጥፍ ነገር አይደለም። በኢትዮጵያ ሕዝቦች የተሰባሰቡትና አንድ የሆኑት በማይሰበር፣ በማይበገር፣ በማይቀለበስ፣ በጠንካራ መንፈስና ወኔ፥ በጋብቻ፥ በጋራ ጥቅም፥ በደምና በታሪክ ተዋኅደው፣ አንዴ አንድ ሆነዋል። ለኔ እንደ ሚመስለኝ፣ ኢትዮጵያዊ ሀገራዊ ጥምር ማንነት (Collective National Identity) ማለት ይህ ነው።

ኢትዮጵያ አገራችን የተመሠረተችው በዚህ ዓይነት ጥልቅ በማይናወጥ ጠንካራ መሠረትና በጥምር ማንነት ላይ ነው። ስለዚህ ኢትዮጵያ መሠረቷ በበለጠ ጠንካራና አስተማማኝ የሚሆነው፣ ተቃናቃኝም ተስፋ የሚቆርጥ፣ ብሔር ብሔረ ሰቦቿ ሁሉ በእኩልነትና በመፈቃቀድ ላይ የተመሠረቱ ሲሆኑ ነው። ይህ አባባል አዲስ ፍልስፍና ሳይሆን ከጥንት ጀምሮ ነበረ፤ ነገር ግን አሁን ይፋ ይሁን፣ ይውጣና ዓለም ይወቀው፤ ይታደስ ነው እየተባለ ያለው እንጂ ሌላ አይደለም። ኢትዮጵያ በዚህ መልኩ ሕዝቦቿን ሁሉ በእኩልነትና በሕግ አቅፋና ደግፋ፣ ያሏትን ጸጋና በረከት፥ እሴቷን ለልጆቿ ስታካፍል ደግሞ፣ አንድነቷ ይበልጥ፥ እንደ ብረት መሰሶ ይጠነክራል።

ብሔር ብሔረ ሰብ ሕዝቦች እኩልነት ሲጓደልባቸው፣ አንዱ እንደ ምርጥ ታማኝ ኢትዮጵያዊ ሲታይ፣ ሌላው ተጠርጣሪ ሲሆን፤ አንዱ ተጠቃሚ፣ ሌላው የዳር ተመልካች ሲሆን፤ አንዱ የእናት ልጅ፥ ሌላው የእንጀራ ልጅ

ሲሆኑ ግን፣ ችግር ይፈጠራል። እንደዚህ ሲሆንባቸው ብሔራዊ መድሎና ጭቆና ደርሶብናል በማለት ሕዝቦች ያማራሉ ማለት ነው። ከዛም አልፎ ጥምር ሀገራዊ ማንነታቸውን አንድነታቸውን ለመናድ ሳይሆን እንደገና ለማደስ በፀረ ጭቆና ያምፃሉ። ብሶትና ጭቆና ባለበት ሁሉ ይህ ነገር ሊሆን ግድ ነውና በኢትዮጵያ በ66 ዓ/ም ፈጦ የወጣው እውነትም ይህ ነበር። ስለዚህ ከዚህ በላይ የተገለፀውና ኢትዮጵያን በዋናነት ያዋቀረው (Makeup) አሠራር ለዘመናት ስለተዳከመና እድሳትም ስላስፈለገው ነበር ብሔር ብሔረ ሰብ ሕዝቦች ጥቅማችንና መብታችን ይከበር፤ ያረጀው ያፈጀው ኋላ ቀር ዘውዳዊው ሥርዓት በዲሞክራሲ፥ በሕዝባዊ አሠራር ሊትካ ይገባል፤ የሥልጣን ባለቤት ሕዝብ ነው በማለት ነበር ሀገር አቀፍ ትግል ሊጧጧፍ የቻለው። ሕዝብ ላነሳው ጥያቄ ያነው መልስ የሚሰጥ፣ ወይም ትግሉን የሚመራና አቅጣጫ የሚያስይዝ፣ የተደራጀ አካል ወይም ኃይል ግን አልተገኘም ነበር። ትግሉ ከባድና ውስብስብ የሆነውም በዚህ ምክንያት ይመስለኛል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ገና-ገና ከጧቱ፣ የዲሞክራሲ መብቴ ይከበር፤ የሕዝብን ፈቃደኝነትና ውህደት የግዛት አንድነትና የመልክዐ ምድር አንድነት አይተካውም፤ "ምንም ብቀጥን ጠጅ ነኝ፤" ሰብአዊ መብቴ፥ ልዑላዊነቴ ይጠበቅ፤ ድምፄ ይከበር በሚል መልክ ነበር ማኀበረ ሰብም ከተቸከለበት ለማንቀሳቀስና ለለውጥ ሕዝብ ጥያቄውን ያቀረበው። ዓለም በፈጣን ዘመናዊ የለውጥ መንኮርኮር እየነጎደች፣ እኛ ግን <<ባለህበት ረግጥ>> ዓይነት ሰልፍ ቆመን ኋላ ቀርተናል፤ እናም፥ እኛም እንለወጥ፣ ሰላለና የለውጥ ፍላጎቱን በሰላማዊ መንገድ ስለገለፀ፣ መሪዎቹ፥ በተለይ ደርጋውያን የገዛ ሕዝባቸውን እንደ ጠላት አሳደዱ በቀይ ሽብር መቱት።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሌ ልዑላዊነቱን፥ ክብሩንና ማንነቱን፥ ሰላሙንም የሚነካበት አይወድም። ወንዘና ተራራ ሁሉ ህዝብ የሚኖርበት፣ አገሬ፥ መኖሪያየ፥ ክብሬ ብሎ በየጊዜው እስከ ደም ጠብታ ድረስ እየከፈለ ህዝብ የሚጠብቀው ሀገርና ዳር ድንበር መሆኑ ግልፅ ነው። ሕዝብና አገር ነጣጥሎ ማየት ባይቻልም፣ ልዑላዊ ሕዝብ ማለት በአንድ ጥምር ማንነት ዓይን ሲታይ፣ የየራሱ ሕግና ሥርዓት፥ ሥነ ሕዝብ፥ ማኅበራዊ ሕይወት፥ ባህልና ታሪክ ያለው ሕዝብ ማለት ብቻ ሳይሆን <u>ምልአተ ሕዝብ</u> ማለት ነው። ምልአተ ሕዝብ ማለት <u>ልዑላዊ ሀገር</u> ማለት ሲሆን፣ ልዑላዊ ሀገር ማለት ደግሞ <u>ሕገ መንግሥታዊ አስተዳደርና አደረጃጀት</u> (Constitution and institution) አንድ ያደረገው <u>ልዑላዊ ሕዝብ</u> ማለት መሆኑን የሚያመለክት ሐቅ ይመስለኛል።

በምልአተ ሕዝብ የዳበረ ልዑላዊነት ደግሞ ካለ ሕዝባዊ ሕገ መንግሥታዊ ቃል ኪዳን ውልና ሰነድ ምንም ትርጉም ሊኖረው አይችልም። በመሆኑም ኢትዮጵያውያን በሰለጠነ አስተሳሰብ፥ በእኩልነት፥ በመፈቃቀድ፣ በመግባባትና በጋራ ጥቅም (mutual benefits) ሁሉም እጅ ለእጅ ተያይዘው፣ በሰላምና በዲሞክራሲ አብረው፣ ተከባብረው የሚኖሩባት፣ ሕገ መንግሥታዊ ዋስትና ያላት፣ ዘመናዊ፥ ሥልጡን፥ ሀገረ ኢትዮጵያን በሕዳሴ ዳግም ለማዋቀርና ለማጠናከር፣ ዜጎች በእልፍ ወአእላፍ ተሰልፈው መተኪያ የሌለው ክቡር ዋጋ፥ ብዙዎች ውድ ሕይወታቸውን ሰውተውባታል፤ በቀጣይነትም እየተሰዉላት ነው። አሁን ያለን ነፃነት፥ ሰላምና ልማታዊ መንግሥት የማንም ገፀ በረከት አይደለም። የተጀመረው ሰላም፥ ዲሞክራሲ፥ ልማትና የሀገር ግንባታ ሥራ ቀጣይና አስተማማኝ እንዲሆን፤ ለሰብአዊ ክብር ዋስትና፥ የዜግነት መብት እንዲረጋገጥ፤ የመሰብሰብና መደራጀት፥ የመናገር፥ የመጻፍና መሰብሰብ ዲሞክራሲያዊ መብት ሁሉ እንዲከበር፤ በነጻነት ለመንቀሳቀስ፣ እምነትና ሰብአዊ ጾታዊ እኩልነት የተረጋገጠባት፣ ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን እዉን ለማድረግ በሕዝቦች አንድነትና ውኅደት፥ በጥምር ማንነት ብዕር፥ በቀለም ሳይሆንም በሰማዕታት ደም ጠብታ በተጻፈ ሕገ መንግሥታዊ ቃል ኪዳን ተሰንዷል። ሰነዱ ጠቃሚና ታሪካዊ ከመሆኑም በላይ የሕጎች ሁሉ የበላይ ሕግ ነውና፣ የልዑላዊ ሕዝብ ክብር የሚያውቅ ሁሉ ክብር ሊሰጠው ይገባል። ይህነን የማያከብር ግን የኢትዮጵያ ወዳጅ

አይደለም፤ የሕግ ዋስና ጠበቃ፥ ወይም የሰብአዊ መብት ተሟጋች ነኝ ቢልም አይሆንም። <በአይቴ ኃሊፊኪ ድኅ ተማሂረኪ> መሆኑ ነው።

ልብ ብሎ ላስተዋለው፣ ሰው መሆን እኮ ራሱ ሕግ ነው። እያንዳንዳችን በውስጣችን ባለው እውነት፥ በሕገ ልቦና መልካሙንና መልካም ያልሆነውን ነገር ሁሉ ለይተን ብይን ለመስጠት የሚያስችለን የሥነ-አእምሮ ጸጋ አለን። ችግሩ፦ በውስጣችን ላለው እውነት ክብርና እውቅና ሳንሰጥ ስንቀር ነው። ያኔ በውስጣዊ ስሜታችን የሰው መሆን ክብራችን ሚዛኑ ሲቀል፣ ሲቀንስና ስፍር ሲጎድል ይሰማናል። በሠራነው መጥፎ ነገር እንከፋለን፤ መልካም ነገር ስንሠራ ግን ደስታ ይሰማናል። በዚህ መልክ በመፅሔተ ሥነ-ልቦና ፊት ቆሞ ራሱን የማይመረምር ከሆነ፣ ሰው የሚያሰኘውን ባህርየ ሰብእነት የሌለው፣ ሰው መሳይ እንስሳ፣ ጎደሎ ፍጥረት ነው። በዚህ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም እንሆ ዛሬ ሰውን እንደ እንስሳ የሚጠብቅ መንግሥት የሚሉትን ሎሌ ያስፈለገው። ትልቁ ችግር፥ ሰው ከሰብአዊ ባህርዩ ይልቅ እንስሳዊ ባህርዩ ልቆ ሲጠናወተው ያለማስተዋሉ አሳፋሪ ነገር ይመስለኛል።

አንድ የሕግ አስከባሪ አካል ወይም ሰው ከሕግ ውጭ የሚሄደውን ሌላውን ሰው ጠርቶ፣ አንተ ሰው ተው እንጂ ሥርዓት ያዝ፣ ከሕግ አትውጣ፣ አትተላለፍ ቢለው ይህ ራሱ ላስተዋይ ሰው ስድብና ውርደት ነው። ይህ ነገር ካለማውቅ የተደረገ ተራ ስሕተት ከሆነና ሕግ ተላላፊው መተላለፉን ተረድቶ ቢመለስ፣ ያኔ፥ ለትምህርት ይሆነዋል፤ ባይመለስ ግን ሰብእነቱን ካማዋረዱም በላይ በሕግ ያስጠይቀዋል ማለት ነው። ስለዚህ ሰው ራሱን ለሕግ የማያስገዛ ከሆነ፣ ሰው መሳይ እንስሳ ነው። በዚህ መልኩ ሲታይ፣ ሕገኛ ሁኖ መገኘትና ያለ መገኘት፣ የሰው መሆንና ያለመሆን ያክል ትርጉም አለው ያስብላል። ሕገኛ ሆኖ መገኘት፥ የሕዝብ መብት ማክበር፣ የሕግ የበላይነትን አውቆ መቀበልና ሕግ ማክብር መልካም ነው፣ ያስመሰግናልም። እንዲህ ዓይነቱ ሕግ አክባሪ ሰው ሰላማዊና ሕጋዊ ሰው ብቻ ሳይሆን ሕግ ያከበረው፤ ንኡድ፣ ክቡር፣ ምስጉን ሰው ከመሆኑም በላይ ሕዝባዊም ነው። ፀረ ሰላም፥ ፀረ ሕግ የሆነ ሰው ደግሞ ሰው ከሚያሰኘው ባህርየ ሰብእነት ውጭ ሄዷልና ብእሴ ዓመፃ፣ ፀረ ሕዝብ የሆነ ሰው ነው፤ ምን ጥያቄ አለው።

ለምሳሌ፤ ፀረ ሕዝብ ኃይሎች በኢትዮጵያ ሰላም፥ ሕግና የሕዝብ መብት ማክበር በቀረና እንሆ የሀገሪቱ ደም ሥር የሆነውን የብሔርና ብሔረ ሰብ ሕዝቦች ህልውናም ጭምር <<እኛ የብሔር ብሔረ ሰብ ከረጢት አይደለንም>> በማለት መድረክ ላይ በይፋ ሲክዱት ሰምተናል። አንዴ ወደ ላይ፣ አንዴ ወደ ታች፣ በያዝ ለቀቅ ወለም ዘለም፣ በተውሶ ርዕዮተ ዓለም ግራ ተጋብተው ዚቅበዘበዙም የኢትዮጵያ ሕዝብ አይቷቸዋል። የሚተባበሩበት የጋራ ራዕይና ዓላማ ሳይኖራቸው ኢህአዴግን ማቃወም ብቻ እንደ ዓላማ ወስደው ሲተባበሩ፣ ግን ደግሞ የገፋቸው ሳይኖር ሲገፈተሩና ወድቀውም ሲሰባበሩ ታዘብናቸው። ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን አክብረው፣ የሕዝብን ልብ ትርታ አድምጠው፣ የጎደለውን በሟሟላት፣ አማራጭ ኃይል ሆነው ከመቅረብ ይልቅ ተቃዋሚ በሚል ራሳቸውን በጠላትነት ፈርጀው ከሕግ ማዕቀፍ በወጡ ጊዜ፥ እኔ እንደሚመስለኝ፣ ነገሩ የተበላሸባቸው ያኔ ገና ከጧቱ ነበር።

## ክፍል ፫፥ ታጥቦ ጭቃ ግልገሉ ልዑል፣ መድረ ላይ ሲንከባለል።

በመስፍናውያኑ ጨቋኝ ገዢዎች አመለካከት በሽታ በተለከፉ ሰዎች የሚዘመረው የንቀትና ጥላቻ መዝሙር አዲስ ነገር አይደለም። በአራተኛው ዙር ምርጫ ውድድር ጊዜ ሲቀነቀን የሰማነውም ያው ቅንጅታዊ ዘመናዊ ትምክሕት ነው። የኔው አከባቢ ግልገሉ ልዑል እኔ ነኝ፤ እኔን የሚወዳደር፣ የሚገጥመኝ ሰው አይገኝም እያሉ በትምክሕት አገሱብን። ይህም ያው ቢገለብጡት ወጮ ነው።

ጥንትም ከገዢዎች ባህል በተለየ መልኩ ብሔር ብሔረ ሰቦች የየራሳቸው ባህል ቢያንፀባርቁ፣ ልዩ-ልዩ የሥነ-ቊንጅና መልክ፥ ንቅሳትና ውበት፥ ባህላዊ አለባበስ፥ ምግብና አመጋገብ ወዘተ ያላቸውን ሕዝቦች የኛ አይደሉም፤ እንዲህ ዓይነት ኢትዮጵያውያን ዜጎች የሉነም እየተባሉ፣ ኢትዮጵያዊነታቸው ሲካድ ብዙ ጊዜ ሰምተናል። ታድያ ዛሬ መድረክ ላይ ያንን የተለመደውን ትምክሕትና ክሕደት ቢደጋገም በግራሞት ያሳዝናል እንጂ ምኑ ያስደንቃል።

በተለይ የመድረክ አባል የሆኑት አቶ ስየ አብርሃ፥ «እኛ የብሔር ብሔረ ሰብ ከረጢት አይደለንም» ሲሉ በራሳቸው የአነጋገር ፈሊጥ የጠቀሱትን ነገርና ወደ ኅብረተ ሰብ ያስራጩት መልእክት ሌላ ትርጉምና ማባባያ ካልታከለበት በስተቀር፣ የወጣለት ደረቅ ክሕደት ነው። የአቶ ስየ አነጋገር ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን ታሪካዊ የሕዝቦች አንድነትና ጥምር ማንነትን የሚያላላ ብቻ ሳይሆን በብሔርና ብሔረ ሰብ ሕዝቦች እኩልነትና መፈቃቀድ ላይ የተመሠረተው ፌዴራሉን ሥርዓት፥ ማእከላዊነቱን የሚንድ ደፋር ብቸኛው ዓይን አውጣ፣ የአሐዳውያን አስተሳሰብና ትምክሕተኛ አመለካከት ይመስለኛል። ምክንያቱም፦ በአንድ በኩል ሕገ መንግሥቱን ለመሸራረፍና ለመሸርሸር ዓንቀፅ 39ኙን ሲቃወሙና ሥርዓቱን ለማጨናገፍ ሲዝቱ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የሕዝብ ዜግነታዊ መብት ከመጋፋትም አልፈው ህልውናቸውንም እስከ መካድ መድረሳቸውን ያመለክታል።

ዓንቀፅ 39ኙ ብሔራዊ መድሎንና ጭቆናን ከሥር መሠረቱ የሚያስወግድ ፍቱን ምድኃኒት ከመሆኑም በላይ፣ ሕዝቦች ከጥርጣሬ ተላቀው፣ ብሕዳሴ፥ ኢትዮጵያዊ ማንነታቸውን የሚያረጋግጡበት፣ ዋስትና የሚሰጥ መሰረታዊ ሰነድ መሆኑን ተቃዋሚዎች ሳያውቁት ቀርተው አይደለም። ይህ ከፀረ ሕዝብነት አቋም የሚመነጭ፣ ሕገ መንግሥቱን ዓንቀፅ በዓንቀፅ እየሸራረፉ የብሔርና ብሔረ ሰብ ሕዝቦች መብት መና ለማስቀረት የነደፉት ስትራተጂ ነው። ይህ ራሱ ጦርነት ማወጅ ማለት ነው። ምክንያቱም ካለ ሕገ መንግሥት ሀገር ስለ ማይቆም፣ ሕገ መንግሥቱን በማፈራረስ በሥርዓተ አልበኝነት ሀገር ለማተራመስ እንደ መሞከር ይቆጠራል። ይህ ሓላፊነት በጐደለው አሠራር የሀገር ድኅንነትን አደጋ ላይ በመጣል የሚያስወቅስና የሚያስጠይቅ ታላቅ ግብረ ክሕደት ይመስለኛል።

ተቃዋሚ ድርጅቶች፣ ዓንቀፅ 39ኙን ሲቃወሙት፣ ለአገር አንድነት ተቆርቋሪ መስለው፣ ዓንቀፁ አገር ይበትናል በማለት እንደ ማስፈራሪያ ነገር ሊጠቀሙበት ይሞክራሉ። እውነቱ ግን ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን ኢትዮጵያዊ ሀገራዊ ስሜትን፥ ጥምር ማንነትን፥ አንድነትን ያጠናክራል፣ ያድሰዋል እንጂ አያላላውም። ምክንያቱም ብሔር ብሔረ ሰቦች እውቅና የሰጡበት፣ ተወያይተዉ ያፀደቁት ሕገ መንግሥት ነው፤ በተለይ ዓንቀፅ 39ኙ ያስገኘውን ጥቅምና አንኳር-አንኳር ቁም ነገሩን ባጭሩ ጠቅሶ ማስርዳት የሚቻል ይመስለኛል።

ሀ. ሕዝቡ ያነገበውን ጠመንጃ ጥሎ ወደ ሰላምና ወደ ልማት ፊቱን ለማዞር አስችሎታል።

ለ. ራስን በራስ ለመተዳደር ሙሉ መብት አጎናፅፏቸዋል፤

ሐ. ብሔር ብሔረ ሰብ ሕዝቦች በየክልሉ መክረው ዘክረው የሚያማክላቸውን ፌዴራላዊውን መንግሥት ለማቋቋምና የሥልጣን ባለቤት ለምሆን ችለዋል፤

መ. ዓንቀፅ 39ኙ ባስገኘላቸው ድል ምክንያት ብሔር ብሔረ ሰብ ሕዝቦች ኮርተው፣ ምንም ሳይሸማቀቁ፣ ሳይፈሩና ሳያፍሩ ቋንቋቸውንና ባህላቸውን ለማሳደግ ችለዋል። በቋንቋቸው ለመማርና ለመዳኘት በቅተዋል። ዛሬ በቋንቋው፥ በባህልና በማንነቱ የሚያፍርና የሚሸማቀቅ ኢትዮጵያዊ ብሔር ብሔረ ሰብ የለም። ሁሉም

በየማኅበረ ሰቡ ቋንቋ፥ ባህልና ደንብ ማኅበታዊ አገልግሎት እያገኘ ነው። ይህም የማንም ስጦታ ሳይሆን ሕዝቦች በተጋደሎ ያገኙት ድል ነው። በመሆኑም ሕዝቡን ይህነን ፀጋ ለማጨናገፍ ከመሞከር በላይ የከፋ ፀረ ዲሞክራሲ ኃይል የሚኖር አይመስለኝም።

ሠ. የብሔር ብሔረ ሰቦች መብት ከድተው፣ በአማራጭነት ሳይሆን በተቃዋሚነት፣ በግንባታ ሳይሆን በአፍራሽነት፣ የተሰለፉት ኃይሎች፥ የመድረክ ሰዎች፥ መለስተኛ ቅንጅት፥ እነ አቶ ስየ፥ ከላይ እንደ ተገለፀው "*…እኛ የብሔር ብሔረ ሰብ ከረጢት አይደለንም…*" በማለት በደፈናው ሲከዱዋቸው ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱ ራሱ ጠበቃ ቆሞላቸዋል። ስለዚህም ተቃዋሚዎች ዓንቀፅ 39ኙን በተለይ፣ ሕገ መንግሥቱን ግን በአጠቃላይ፣ አምርረው ይጠሉታል፣ ይሸሹታልም።

አቶ ስየ «ከረጢት» ሲሉ የኢትዮጵያ ኅብረ ብዙኅንትን ስለማያውቁ ነውን? ኅብረ ብሔራዊቷ ሀገር ኢትዮጵያ ከ80 ቋንቋዎች በላይ የሚነገሩባት ታላቅ አገር ናት። ታድያ አቶ ስየ ሕዝቦቿን በንቀት እንዲሁ አሳንሰው ካልተመለከቷቸው በስተቀር፥ ኢትዮጵያ ሀገራችን ከረጢት አይደለችም። አቶ ስየ ይህች ታላቅ የታላቅም ታላቅ አገር፣ ኢትዮጵያን ይህነን ያክል አናንቀውና አሳንሰው ከረጢት ከሚሏት ይልቅ በሌላ መልክ ክብር ሰጥተው፣ ተለቅ ባለ አንድ ነገር መስለው፣ ቢጠሯት ለራሳችውም በተሻለቸው ነበር። ነገር ግን ፊውዳላዊ አንገተ ገትር ባህርያቸው ስላልፈቀደላቸው ሊሆን ይችላል፣ አቶ ስየ በድፍረት ሕዝቦቿን በሙሉ አንድ ላይ ጨፍልቀው በከረጢት መሰሏት፣ ደፈሯትም። ያ ድፍረት ደግሞ የኢትዮጵያን ሕዝብ ልብ ያደማው ታላቅ በደል ይመስለኛል። ዓፀፋውም ያው፥ የተከበሩብትን ያክል ተዋረዱ፤ የተወደዱበትን ያክል ተጠሉ። ያ ባይሆን ኖሮ ግን ባይመረጡ እንኳ የሚቆጠር ድምፅ ባከኙ ነበር።

አቶ ስየ "እኛ የብሔር ብሔረ ሰብ ከረጢት አይደለንም" ሲሉ የተናገሩትን አጉራ ዘለልና ልቅ አነጋገር በተቃራኒው ወስደን ስንመለከተው ግን ኢትዮጵያ ከረጢትነቷ በመጠን ሳይሆን በዓይነትና በይዘት ኅብረ ብዙኅነቷን የሚያሳይ ጥሩ ምሳሌ ነው የሰጧት፣ አቶ ስየ። አባባላቸው በትዕቢትና በከሐዲነት መልኩ የተሰነዘረባት ቢሆንም እንኳ፥ ኢትዮጵያ በተለያዩ ኅብራውያን ዓይናማ እምቡጥ አበባዎች፥ በብሔር ብሔረ ሰብ ሕዝቦች፥ ያሸበረቀች ከረጢት ናት፤ የተሞላችውም ወርቅ በሆኑት ሕዝቦች ነው። ይህ ደግሞ ለኢትዮጵያ ሕብረ ገጽቷንና ይዞቷን የሚያሳይ ያልተጋነነና ያልወገነ እውነተኛ ትርጉም ምስሎ ይታየኛል።

አነጋገራቸው ግን ክሕደትና ድፍረት ከመሆኑም ባሻገር፥ አቶ ስየ፥ በትምክሕተኞች ጎራ ርካሹና ውዳቂውን የጥላቻ ፖለቲካ ርፍራፊ ለማግኘት አስበው የሰነዘሩት አነጋገር ለመሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነገር ነው። አዎ! ወያኔን ወያኔዎች እያሉ እያብጠለጠሉ፣ የብሔር ብሔረ ሰቦች ክብር ካልዘነጠሉ፤ ሕገ መንግሥቱን በይፋ መድረክ ላይ ወጥተው ካልተቃወሙና ካልተራገሙ፤ የሕዝብ ጥቅምና እውነቱን ካልከዱ፤ አቶ ስየ በደርገ ኢሠፓ ቅሪቶች፣ በቅንጅቶች፥ በአገር አፍራሽ ከሐዲ ጎራ ተቀባይነትና እምነት ሊኖራቸው፣ ሊታቀፉም አይችሉም። አቶ ስየ ለመወላገዳቸው ኢምክኑይ ምክንያት የሚመስለኝ ይህ ነው። እንዲህ አድርገውም ቢሆን አቶ ስየ እንዳው በለስ ቢቀናችው ነው። ምክንያቱም በትምክሕተኞች ቤት ትግሬ መሆን ራሱ ኃጢአት ነውና አቶ ስየም ከትግሬነትም በላይ የወያኔ ታጋይ ነበር አበሳ ተጨምሮባቸው፣ "እንኳን ዘንሞብሸ ድሮዉም ጤዛ ንሸ" እንዲሉ፣ ቀድሞውም ቢሆን ትግሬ አይታመንም በሚል የተለመደ ዘረኛ አመለካከታቸው አቶ ስየ አብርሃን ክፉኛ አበሳጭተው ሲያባሯቸው፣ አኝከው ሲተፏቸው፣ ሲኑቋቸው፣ ሲሰድቧቸው፣ ሲያዋርዷቸውና ቁም ስቅል ሲያሳዩዋቸው የምናይበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም።

እንደ ዛሬ አያድርገውና፣ አቶ ስዩ ቀድሞ የኢህአዴግ ታጋይ ባለሥልጣን በነበሩበት ወቅት፥ ዓንቀፅ 39[ኝ] ኢትዮጵያን የሚገነጣጥላትና የሚያፈራርሳት ሳይሆን ሕጉ ለኢትዮጵያ አንድነት *«የመአዝን ድንጋይ ነው»* ሲሉ እንዳልተደመጡ ሁሉ፣ ያኔ ያወደሱትን የመአዝን ድንጋይ መድረክ ላይ ድንገት ሲከዳቸውና ሲገለባበጥባቸው፣ ሲያዳልጣቸውም ጊዜ፣ የወታደር ነገር፥ ቀኝ ኋላ ዙር ፖለቲካ ረገጡብን። ከ17 ዓመት በላይ በታጋይነትና በመሪነት ደረጃ የብሔር ብሔረ ሰብ መብት ለማስከበር በሚል ዓላማ የታገሉለትን መርሕ ድንገት አሽቀንጥረው ጣሉት። *<ታጥቦ ወደ ጭቃ>* እንዲሉ አቶ ስዩ ሕዝብ የሠጣቸውን የታጋይነት ክብር አውጥተው ጣሉት፤ እንደ እርያ ጭቃ ላይ ረገጡትና ተንከባለሉበትም።

ክፍል ፬፡- የአቶ ስዩ ፖለቲክስ፡-

ኢትዮጵያ ዓለም አቀፋዊ፣ አህጉራዊና ሀገራዊ ግዴታዋን ለመወጣት በሰላም አስከባሪ ተልእኮ (Peace keeping task) የምታካሂደውን እንቅስቃሴ አቶ ስዩ ገልብጠው በአሉታ በመተርጎም ወደ ፅንፈኛ አቅጣጫ ለጠጡት፡-

፩[ኛ]. በዲፕሎማሲው ዘርፍ ችግር ለመፍጠር በንግግራቸው ከዓለምና ከጎረቤት አገሮች ጋር ለማጋጨት ሞክረዋል።

፪[ኛ]. ነገሩን ከሃይማኖት ጋር በማላከክ ፀረ ሀገር አቋም መያዛቸው በምርጫው ጊዜ ንግግራቸው ተስተውሏል።

፫[ኛ]. ኢትዮጵያ በሶማልያ፥ በዳርፋርና በሌሎችም ሀገሮች ያላትን የሰላም አስከባሪ ተልእኮም በጣልቃ ገብነት መልክ በመተርጎም ሲኰንኗት ተደምጧል፤ እናም፥ አቶ ስዩ ከአነጋገራቸው *"ባልበላውም ለምን ጭሬ አፈሰውም"* አለች ደሮ ዓይነት፣ ለማብለሸት ሆን ብለው ያደረጉት ነገር ይመስለኛል።

፬[ኛ]. የኢትዮጵያ መንግሥት የአሜሪካ ቅጥረኛ ነው በማለት ወንጅለዉታል። እውነቱ ግን *<የአብዬን እከክ ለእምዬ>>* ሆኖ እያለ፣ ቂጣና ኃይለ ቃል በታከለበት ውሸት መቅላመድና ድብብቆሽ ከታጋይ ነበር ሰው፣ ከአቶ ስዩ ይጠበቃል ወይ?

አይጣል! አይጣል ነው እንጂ፡- ...እኮ! የታጋይነት ሕብሩ ካልለወጠና ሕዝባዊ ባህርዩ ካልተገለበጠ በስተቀር፣ ታጋይ በኵርፍያ፥ በቂም-በቀል፥ በስስት፥ በሙስና፥ በክሕደትና በአውቆ አጥፊነት አይጠረጠርም ነበር። ክፋት፥ ምቀኝነት፥ ተንኮል፥ ፍቅረ ንዋይ፥ ሴሰኝነት፥ ትዕቢት፥ አጉል ጉራ፥ ቂጣና ቅሌት ከታጋይ ነበር አይጠበቅም፤ ያልተለመደ ነግር ነው።

ከእውነተኛ ሕዝባዊያን ታጋዮች በተግባር ያየነው፣ ታጋይን ታጋይ የሚያሰኘው ልዩ-ልዩ መስፈርት አለው፡- ታጋይ ራሱን፥ ጊዜውን፥ እውቀቱን፥ በመጨረሻ ባመነበት ዓላማ በፅናት ተሰልፎ፣ ውድ ሕይወቱን ሳይሳሳ፣ ለሀገር ለወገን ቤዛ የሚሰጥ-የሚሰዋ ነው። እውነተኞች ታጋዮች መስዋዕትነት በመጣችበት ሁሉ ይቀበሏታል እንጂ አይሸሿትም። ለታጋይ መስዓዕትነት የሚመረጥ መልክ፥ የዓይነትም ዓይነት፥ ስፍር ወይም ቍጥር የለዉም። መታሠር፥ መንገላታት፥ መተቸት፥ ሂስና ግለ-ሂስ፥ እርምት የማይቀር ነው። ታጋይ እስከ ሆኑ ድረስ አካላዊ ጉዳት፥ መራብ፣ መጠማት፣ እርዛት፥ ሌት ተቀን ውጣ-ውረድ ጉዞ፥ ድካም፥ የጉልበት ሥራ፣ ሌላም-ሌላም ብዙ ሀገራዊና ድርጅታዊ ሐላፊነት በተአማኒነት መወጣት፣ ...አረ ስንቱ! ታጋይ የህነ ሰው በከባድ

የትግል ፈተና ይፈተናል። ትግሉ ትግል ያሰኘውም እኮ ይህ ነው። ታድያ፥ አቶ ስየ ይህነን ሁሉ ፈትና ተወጥተዉታል ማለት ነው ወይ? ወይስ ስለ ታሠሩና ስለ ተደፈሩ አኵርፈው ወደ ቂም-በቀልና ወደ ብቀላ ገብተዋል? ማንን ነው የሚበቀሉት? ሕዝቡን? ታጋዩን? ድርጅቱን? ለምን? ፍርዱ ለናንተ እተዋለሁ።

ለመሆኑ አቶ ስየ አብርሃ በትግሉ መርተው ያስዉያቸውን ሰማዕታት፥ የሕዝብ ልጆችና የትግል ቃል ኪዳን ጓዶቻቸውንስ መቼውኑ ተረሷቸው? ይህ አሳፋሪ ነገር የክሕደት ክሕድት ከመሆኑም በላይ "ከአንድ ራስ ሁለት ምላስ" የሚሉትን አባባል ያስታውሰናል። ለካ΄ስ ሰው አይታመንም! <ሰውን ማመን ቀብሮ ነው፤> ይላል ያገሬ ሰው። እነ አቶ ስየ እንደ ጲላጦስ በመጨረሻዋ ሰዓት ሀገርን፥ ሕዝባዊ ጥምር ማንነትን፥ እውነትን፥ የሰማዕታት ታጋዮች ቃል ኪዳን ከዱ፤ የቅጥረኞችና ምንደኞች ሀገር አፍራሽ ማኅበር ፅዋ ጠጡ። መጠጣት ብቻም አይደለም፦ አቶ ስየ አብርሃ፥ አደግድገው ዋና አሰላፊ፤ አቶ ገብሩ፥ የእልፍኝ አስከልካይ ዋና አጋፋሪ፤ ወ/ሮ አረጋሽ አዳነ ደግሞ ጌቶች የጠጡበትን ፅዋዕ አጣቢና አድራቂ በመሆን፣ ደርገ ኢሰፓውያንና ቅንጆቶች ጌቶቻቸውን አገለገሉ። ቅራሬውን የሚጨልጡ፣ አተላውንም የሚያሽቱ፣ ጥቂት ቆልባጭ ወራዳ ጀሌዎችም አልታጡም። ይህ ግን የጸሓፊው በይነ ትዕዝብት ብቻ ሳይሆን ሕዝብ በሚሰበሰብበት ቦታና በየዓውደ ምኅረቱ ሁሉ ብዙዎች የሚጋሩት፣ መነጋገርያ፥ ወቅታዊ ርእሰ ጉዳይ ነው።

የአቶ ስየ ነገር ግን እያደረ ያስገርማል፦ ሰውየው የፖለቲካ ብስለቱ፥ የዓላማ ፅናቱ፥ ሕግ አክባሪነቱ፥ ሕዝባዊነቱ፥ የሀገር ፍቅር ወኔው፥ የተጋድሎ ልምዱና ጀግንነቱ ምን ጊዜው ውሃ በላባቸው? ወይስ ቀድሞውንም ቢሆን እንዳው ብስለት የጎደለው፣ <በጨው ደንደስ በርበሬ ተወደሰ> ዓይነት፥ ለብ-ለብ ስለ ነበረ ነው በሚል በመሪነት ብቃታቸውና በፖለቲካ ሕይወት ሥነ-ስብእናቸው ላይ ከባድ ጥያቄ አስከትሎባቿል። ጥያቄ ብቻም አይደለም፦ ተአማኒነት አጡ፣ ከሕዝቡ ልብ ወጡ፣ በሀገር ደረጃ ቀርቶ በተወለዱባት መንደር እንኳ ውርዴት እንጂ የቋመጧትን የልዑልነት መዓርግ ሊያገኟት አልቻሉም።

አቶ ስየ በሌሎች ትክሻ ላይ ተንጠልጥለው ይሆን ያነን ያኽል ዘመን የኖሩት? ያነን ያክል ርቀት ግን እንዴት




ሊጓዙት ቻሉ? ወይስ ይህ ታጋይ የነበረው ስየ ሳይሆን ሌላ ስየ ነው? ይገርማል። አቶ ልደቱ አያሌው ስለ አቶ ስየ አብርሃ በድኅረ ገጽ ባስነበቡን ጽሑፍ ላይ፥ 40 ዓመት ባሕር ውስጥ የኖረው ድንጋይ ምንም ቂዕ የሚል ርጥበት አይወጣውም በማለት ግራሞታቸውን የገለፁበት ምክንያት ይህነን በማስተዋል ሳይሆን አይቀርም። ድንጋዩ ግን ተለቅልቆ ተለቃልቆ ወጣ እንጂ ርጥበት በቀረውና ታጥቦ ቢነጣ እንኳ ባልከፋ ነበር። የሚገርመው ነገር ግን ድንጋዩ ጭራሹም ውሃ የነካው አይመስልምና በየቤቱ የድንጋዩ ነገር ብዙዎችን ያስገረመ፤ አየ ሰው! የሚሰኝ ወቅታዊ ትዕዝብትና ግንዛቤ ይመስለኛል።

በአቶ ስየ ብቻም ሳይሆን በአጠቃላይ የአቶ ልደቱ ግንዛቤ እውነተኛነቱ በ4ኛው ዙር ሀገራዊ ምርጫ ጊዜ ተረጋገጠ። ሕዝብ ፍርዱ ሠጠ፤ ራዕይ ያለውን፣ በሰላምና በሕግ አክባሪነት፥ በሀገራዊ መሠረተ ልማት ግንባታ የማያወላውል ፅናት ይሆነኛል፤ ከድኽነትና ኋላ ቀሪነት መርቶ ነጻ ያወጣኛል፤ ታግሎም ያታግለኛል ያለውን፤ በተግባር፣ የሕዝብ አለኝታ፣ የሀገር መከታ ሁኖ ያገኘውን ፓርቲ፥ ኢህአዴግን ወዶ መረጠ። መምረጥ ብቻም ሳይሆን ወሰነ። በመጨረሻም እንደ ሕዝብ <<ምንም ብቀጥን ጠጅ ነኝ>> ምንም ብደኽይም ሕዝብ ነኝ፤ ድምጼ ይከበር፣ ሲል የኢትዮጵያ ሕዝብ በሀገር አቀፍ ደረጃ ሰላማዊ ሰልፍ ወጥቶ፣ የሩቁም የቅርቡም ሕግ ተላላፊዎቹን ሁሉ በአንድነት ድምፁ አስጠነቀቃቸው። በዚሁ ታሪካዊ ፍጻሜ ምክንያት እንሆ ጉንቦት ፲፭፥ ፳፻፪ት ዓ/ም ታሪካዊ ዕለት ሆነች። የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ እውነተኛ ማንነቱን፥ አንድነቱን፥ ሕጋዊነቱን፥

በሳልነቱን፥ ጨዋነቱን አሳየ። በዚህ በእትዉ በሰላም መልኩ የምርጫ ጉዳይ አለቀ፤ በቃ! ሕዝቡ ራሱ አጠናቀቀው።

**ፍጻሜው፦ የባለ ብዕሩ ልሳን፦**

ስለ ኢትዮጵያ ሀገራችን ወቅታዊ ሁኔታ፥ በተለይ በምርጫው ጊዜ ዘመን ባፍራው ኮምፒዩተርና ቴሌቭዥን፥ በሩቅ-ቅርበት የተከታተልኩትን ነገር ወገኖቼን ለማወያየትና ለመማማር በሚል መሠረተ ሐሳብ ነበረ ይህችን የከተብኳት። ነገር ግን ከብረት ዝገት፥ ከሰው ጉድለት ሁሌ ኢይታጣምና ጉድለቱን፥ ግድፈቱን በእርምት፣ ድፍረቱን ግን በይቅርታ እንድታልፉኝ አብዝቼ እጠይቃለሁ።

ኢትዮጵያ በነጻነት ለዘላለም ትኑር፤
ክብር፣ ምሥጋና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይሁን፤
ክብረ ሞገስ ወ ዘለዓለማዊ ዝክር ለሰማዕታት ፳ ግንቦት።

ፋሽሽታዊ ደርግ እንደ ተሸነፈ ሁሉ፣

ድኽነትና ኋላ ቀርነትም ድባቅ ይመታሉ!!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!

አሜን!

---

ሊበራሊዝምን በተመለከተ፣ ሌላ ርዕስ ይዤ እመለሳለሁ
እስከ ዚያ ድረስ በድህና ሰንብቱልኝ።